# የምን ዘር-ማንዝር ?

የጐንቻው!

የምን ዘር-ማንዝር ጐሣ መቁጠሬ፤
ሰውነቴ እንጅ፤ አትብቴ ክሬ፤
በአገር ማህጸን በሽል አድሬ፤
ተካፍዬ አብራክ ሕይዎት ቋጥሬ፤
ትውልዴ ሰው ነው አፈጣጠሬ፤
ስብዕናዬ ማተቤ ክብሬ፤
**የምን ዘር-ማንዝር መቀባጠሬ።**

ብሆን ከተሜ ወይም ገጠሬ፤
አገው ቤሻንጉል ልሁን ጐንደሬ፤
ኦሮሞ አማራ ጉራጌ ትግሬ፤
ሶዶ ከምባታ ጉጂ ሃደሬ፤
ምስራቅ ምዕራብ ደቡብ መንደሬ፤
ብሆንስ ሰሜን ወለጋ ጅማ ወይም ሀረሬ፤
ልሁን ወሎዬ፤ሸዋ ጐጃሜ፤ኢሉባቡሬ፤
የትም ልወለድ ከእናት አገሬ፤
ሰውነቴ እንጅ እትብቴ ክሬ፤
**የምን ዘር-ማንዝር ጐሣ መቁጠሬ።**

ጸሎት አምልኮ የግል እምነቴ፤
ኃይማኖቴ መንፈሳዊ ኃይዎቴ፤
እድሜ ያታዬ ተፈጥሯዊ ማንነቴ፤
ጸጋዬ እንጅ ጌጤ-ውበቴ፤ መስተዋቴ፤
የዓለም ካባዬ ክብር ቡራኬ ሰውነቴ፤
እንደ ዜጋ በአገሬ የምላበሰው የክቴ፤
የእኩልነት ምልክቴ የሰውነት ኩራቴ፤
**የምን ዘር-ማንዝር ከንቱ መለያያ መሻቴ።**

የዜግነት የአስተዳደር ራዕይ ፍና፤
የምመኘው የጥበብ እድገት ጐዳና፤
የስልጣኔ የምጣኔ ሃብት እውቅና፤
ሳይንስ ምርምር፤ ንግድ ሙያ ባልትና፤
እንዲዳረስ ለሁላችን ፍቅር ሰላምና ጤና፤
**የምን ዘር-ማንዝር ችርቻሮ የወረት ቁና።**

የወያኔው አበሳ ኑዛዜ ስንቱ ተሰልቶ፤
እስከ መቼስ ጠብ-መንጃ አንግቶ፤
በዶማ ስለት የሞገተውን ወግቶ፤
ደም አፍስሶ፤ ንዋይ ኃይዎት ሰውቶ፤
ገድሎ አገዳድሎ፤ ትውልድ በደም አቃብቶ፤
በሙታን አጽም የዘር መሰላሉን አቅንቶ፤
የበቀል ሥርዎ-መንግስት መሥርቶ፤ዙፋን ወጥቶ፤
ድምጽ በአፈሙዝ ቀምቶ ሕዝብ ባሳር አግቶ፤
ከሰው ከፈጣሪው ከኃሊናውም፤ ሸፍቶ፤
ከስጋ ከመንፈሱ ተጣልቶ ሁለመናውን ጐድቶ፤
ከፍሎ እማይዘልቀው የትውልድ አራጣ ገብቶ፤
ያምጣል ማጥ አርግዞ የጥፋት እድር ጠጥቶ፤
እጸ-ፋሪስ፤የኰሶ-ጉሽ ተግቶ፤በግፍ ቁንጣን አቃስቶ፤
በልቶ የቀን በለስ ከዓመት ዓመት አቃቶ፤
እንደባነነ ዘወትር ሰላም እንቅልፍ አጥቶ፤
**እስከመቸ ይኖር ይሆን? ዘር-ሸምቶ፤ ዘር-አቅንቶ።**

• በዘር ማንዝር ደዌ ለተለከፉ ጥንፈኞች አደብ እንዲገዙ ማስታገሻ ትሁንልኝ!!!!! የጐንቻው!

yegonchw@yahoo.co.uk
January 2013